## የንግድ ተሽከርካሪ ህገ ደንብ 13/001 አጠቃላይ ዕይታ

እባክዎ የሚከተለውን ፅሁፍ ይመልከቱ፡-

የንግድ ተሽከርካሪ ህገ ደንብ 13/001 በያዝነው በ2019 ዓ.ም. ግምገማ እየተደረገለት ይገኛል። የሚከተለው በህገ ደንቡ ላይ የተደረገ አጠቃላይ እይታ ህብረተሰቡ በህገ ደንቡ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ማብራሪያ ነው። የህብረተሰቡ ምላሽ መሰረት አድርጎ በህገ ደንቡ ላይ ማሻሻያ ሊኖር ስለሚችል፤ የግምገማው ጊዜ እንዳለቀ ይህ ሰነድ ጠቀሜታ አይኖረውም። እንደአጋጣሚ ሆኖ በዚህ የማብራሪያ ሰነድና በዋናው ደንብ መካከል ልዩነት ከተገኘ ዋናውን ህገ ደንብ ተመራጭ አድርጎ መጠቀም ይቻላል።

- የንግድ ተሽከርካሪ ህገ ደንብ ታክሲን፣ መለስተኛ አውቶቡስን፣ ሊሞዚንና፣ ማንኛውም በውድ ባፋሎ Regional Municipality of Wood Buffalo (RMWB) ግዛት ውስጥ በክፍያ የመጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችን ያካትታል።
- ዋናው የታክሲ መርማሪና የህገ ደንቡ አስከባሪ ኦፊሰር፤ ህገ ደንቡን መሠረት ያደረገ ማንኛውንም ውሳኔ እንዲወስኑ ከከተማው አስተዳደር ስልጣን ተሰጥቷቸዋል።
- አሽከርካሪዎች የሚከተሉትን ስልጠናዎች እንዲወስዱ ሊጠየቁ ይችላሉ፡-
  - የአሽከርካሪዎች የደህንነት ስልጠና
  - በመከላከል የማሽከርከር ስልጠና (defensive driving)
  - የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስልጠና
  - የደንበኞች ግልጋሎትና የሰብአዊ መብቶች ስልጠና
  - የውድ ባፋሎ አካባቢን የማሳወቅ/ በካርታና ቱሪዝም ስልጠና
  - አካል ጉዳተኛ የሆኑ ደንበኞች የማጓጓዝ ስልጠና
  - የተሽከርካሪ አያያዝ፣ ጥንቃቄና ደህንነት ስልጠና እና ሌሎችም ህገ ደንቡ የሚጠይቃቸው ሃላፊነቶች ስልጠና
- የንግድ ተሽከርካሪው ህገ ደንብ ላይ ለውጦች ሲኖሩ፤ አሽከርካሪዎች ተቀጥረው ለሚሠሩባቸው ድርጅቶች የኢሜል መልእክት እንዲደርስ ይደረጋል። ድርጅቶቹም ማንኛውንም ለውጥ ለአሽከርካሪዎቻቸው የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው። በድርጅት ሳይታቀፉ በግላቸው የሚሰሩ አሽከርካሪዎች የኢሜል መልእክቱ ይደርሳቸዋል።
- የሾፌርነት ፈቃድ ለማውጣት፡-
  - ማመልከቻውን ከሚያስፈልገው የአገልግሎት ክፍያ ጋር ማስገባት ይጠበቅብዎታል
  - ከአልበርታ ግዛት የተሰጠ 1ኛ፣ 2ኛ ወይንም 4ኛ ደረጃ የመንጃ ፈቃድ ሊኖርዎ ይገባል
  - በቅርብ ጊዜ የወጣ የወንጀል ነፃ ምርመራ ማድረገዎን የሚያሳይ ወረቀት ሊያቀርቡ ይገባል
  - በቅርብ ጊዜ የወጣ የአሽከርካሪነት ታሪኮን የሚገልፅ ወረቀት (Drivers Abstract) ሊያቀርቡ ይገባል
  - ከሚሰሩበት ወይንም ሊሠሩ ካሰቡብት የታክሲ ወይንም የትራንስፖርት ድርጅት ደብዳቤ ማቅረብ እና የሚሰራ የኢሜል አድራሻ ሊኖርዎ ይገባል።
- የሾፌርነት ፈቃዱ ለአንድ አመት ብቻ ሲያገለግል ንብረትነቱም የከተማ አስተዳደሩ ነው።
- የሾፌርነት ፈቃዱ የግል ንብረቶ አይደለም፤ ፈፅሞ ለሽያጭ ሊውል አይችልም። ከታገደ፣ ከተሰረዘ ወይም የአገልግሎት ጊዜው ካለፈ ለከተማ አስተዳደሩ ሊመለስ ይገባል።
- የሾፌርነት ፈቃዱ የአገልግሎት ተጠቃሚዎችና የታክሲ ተቆጣጣሪዎች ሊያዩት በሚችል ቦታ ላይ ሊቀመጥ ይገባል።
- የሾፌርነት ፈቃዱ ማንኛውም አሽከርካሪ የንግድ መኪናን ወይም ታክሲን ለሌሎች የታክሲ ድርጅቶች ተቀጥሮ እንዲሰራ የሚያስችል ፈቃድ ነው።
- የንግድ ተሽከርካሪ ወይም የታክሲ ፈቃድ ለተሽከርካሪው ማለትም ለታክሲ፣ ለአካል ጉዳተኞች ማጓጓዣ መኪና፣ ለመለስተኛ አውቶቡስና ለሊሞዚን የሚሰጥ ነው።
- የንግድ ተሽከርካሪ ወይም የታክሲ ፈቃድ ለማግኘት፤
  - ማመልከቻ ከሚያስፈልገው የአገልግሎት ክፍያ ጋር ማስገባትም ያስፈልጋል
  - መኪና ሊኖርዎት ወይም በሊዝ ሊያወጡ ይገባል

- ➢ መኪናውን ለስራ ወይም ለንግድ እንዲውል ማስመዝገብ ይጠበቅብዎታል
- ➢ በየስድስት ወሩ ከክፍለ ሃገሩ ውጪ የሚባለውን የመኪና ምርመራ (out of province inspection) ማድረግ ይጠበቅብዎታል
- ➢ ከሚሰሩበት ወይንም ሊሠሩ ካሰቡበት የታክሲ ወይንም የትራንስፖርት ድርጅት ደብዳቤ ማቅረብ ይጠበቅብዎታል
- ➢ መኪናዎ የሶስተኛ ወገን የሁለት ሚሊዮን ዶላር ዋስትና (third party liability insurance) ያለው መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ ይጠበቅብዎታል
- ➢ መኪናዎ በትክክል የሚሠራ የክፍያ መሳሪያ (interact machine) ሊኖረው ይገባል
- ➢ የመኪና ምርመራ የተደረገበት ወረቀት ከሚመለከተው አካል ሊያቀርቡ ይገባል

- የግሎን የንግድ ተሽከርካሪ ወይም የታክሲ ድርጅት መክፈት ከፈለጉ፤ የንግድ ድርጅት ፍቃድ ሊኖረዎ ይገባል። ፈቃዱም ሁልጊዜ በመኪናዎት ውስጥ ለሁሉም ሊታይ በሚችል ቦታ ሊቀመጥ ይገባል። ድርጅትዎም በህገ ደንቡ የተዘረዘሩ ህጎችን ሊጠብቅ ይገባል።
- ነፃ የባለቤት አሽከርካሪነት ፈቃድ የሚሠጠው ለታክሲ ድርጅቶች፣ ተቀጥረው ለማይሰሩ ሰዎች ነው። እነዚህም ሰዎች በቀን ውስጥ 12 ሰዓት ብቻ የሚሰራ የሹፌር ፈቃድ ያለውን ግለሰብ መቅጠር ይችላሉ። የሹፌር ፈቃዱ ሁልጊዜ በመኪናው ውስጥ ለሁሉም ሊታይ በሚችል ሁኔታ መቀመጥ ይኖርበታል።
- ዋናው የታክሲ መርማሪ ወይም ተወካይ ለሹፌር ፈቃድ አምልካቾች ወይም ፈቃዱ ላላቸው ሾፌሮች ማመልከቻቸው ተቀባይነት ካላገኘ ወይም ፈቃዳቸው ከተሰረዘ እንዲሁም ቅድመ ሁኔታ ከተቀመጠባቸው ምክንያቱን በፅሁፍ ዘርዝሮ ሊያሳውቃቸው ይገባል።
- ማንኛውም የሹፌር ፈቃድ የተከለከለ አመልካች በ14 ቀናት ጊዜ ውስጥ በፅሁፍ ለሚመለከተው አካል ይግባኝ ማለት ይችላል።
- ሁሉም የንግድ አገልግሎት የሚሰጡ መኪኖች ወይም ታክሲዎች ውጫቸውና ውስጣቸው በንፅህናና በጥሩ ሁኔታ የተያዘ ሊሆን ይገባል። ዕቃ ማስቀመጫ (trunk) የመንገደኞች ሻንጣ እንዳይበላሽ ንፅህናው የተጠበቀ ሊሆን ይገባል። ተለዋጭ ጎማዎች ከዕቃ ማስቀመጫው ስር ካለው የጎማ ማስቀመጫ ውስጥ ሊቀመጡ ይገባል። የመኪኖችም ዙሪያ በደንብ የታደሠና ከሚታይ ጭረት ነፃ ሊሆኑ ይገባል። አራቱም የመኪና የጎማ ቸርኬዎች (rims) አንድ አይነት ሊሆኑ ይገባል።
- እያንዳንዱ የንግድ መኪና ወይም ታክሲ የውጪውንም የውስጡንም ሁኔታ በግልፅ በመቅረፅ ማስቀመጥ የሚችል የሚሠራ ካሜራ የተገጠመለት ሊሆን ይገባል።
- ከመንገደኞች የሚነሳ ማንኛውም የደህንነት ጥያቄና ተዛማች ጉዳዮች ሲኖሩ እንዲሁም ለምርመራ ካስፈለገ፤ የደንብ አስከባሪ ኦፊሰር የካሜራውን ቅጂ (footage) መጠየቅና መውሰድ ይችላል።
- የታክሲ ድርጅቶች ሾፌሮቻቸው ያሉበትን ቦታ ማወቅ እንዲያስችላቸው መኪኖቻቸው የጂ ፒ ኤስ ሲስተም የተገለጠላቸው ሊሆን ይገባል። የራሳቸው የታክሲ ድርጅት ያላቸው ሹፌሮች ያሉበትን ቦታ የሚቆጣጠር ሶስተኛ ወገን ሊኖራቸው ይገባል።
- ታክሲ ወይም የአገልግሎት መስጫ ተሽከርካሪዎች ከNovember 1 እስከ April 30 የሚቆይ የክረምት ጎማ እንዲኖራቸው ይስፈልጋል።
- ታክሲ ወይም የአገልግሎት መስጫ ተሽከርካሪ ፈቃድ የሚሰጠው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ላሟሉ መኪናዎች ብቻ ነው።
  - ➢ ሦስት በሮች ያላቸው፣ አምስት ሰዎችን የሚያስቀምጡ መቀመጫዎች ያላቸው፣ ስሪታቸውና ሞዴላቸው የታወቀ፣ ከአስር ዓመት በላይ ያላስቆጠሩ፣ የዋጋ ዝርዝር የተለጠፈባቸው፣ ከሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎት ከሚሰጡ መኪኖች ጋር የሚመሳሰሉት፣ የሾፌርና የመንገድኛ መብቶችን የያዘ ባነር የተለጠፋባቸው፣ የሚሰሩበት የታክሲ ድርጅት ዓርማ ያላቸው፣ የመገናኛ መስመር ያላቸው፤ በታክሲ ተቆጣጣሪው እውቀት ያገኙ ማስታወቂያዎች የተለጠፈባቸ፣ በጣሪያቸው ላይ 'ታክሲ' የሚል ምልክት ያላቸውና የሚሰራ የገንዘብ መቀበያ ማሽን ያላቸው
  - ➢ ከከተማ ውጪ የሚሰሩ ታክሲዎች ሜትር አያስፈልጋቸውም
  - ➢ ለአንድ ተሽከርካሪ አካል ጉዳተኞች ማጓጓዝ የሚያስችል ፈቃድ የሚሰጠው የከተማውንና የፌደራል መንግስትን መስፈርት ሲያሟላ ብቻ ነው።
  - ➢ ሁሉም የንግድ ተሽከርካሪዎች ወይም ታክሲዎች የህፃናት መቀመጫን (car seat) በፌደራል መስፈርት መሰረት ማስቀመጥ የሚችሉ መሆን አለበት፤ ደንበኞች የህፃናት መቀመጫ አገልግሎት ከጠየቁ፣ ለአገልግሎቱ 5 ዶላር ማስከፈል ይቻላል።

- የሊሞዚን አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት ተሽከርካሪው
  - ሴዳን ሊሞዚን
  - ዘመናዊና ምቾት ያለው የስፖርት ሊሞዚን
  - ረዥሙ ሊሞዚን ወይም
  - ህገ ደንቡን የሚያሟላ ልዩ የሆነ ሊሞዚን ሊሆን ይገባል።
- አንድ ሊሞዚን በውስጡም ሆነ በውጪ ምንም አይነት ማስታወቂያ ሊለጥፍ አይችልም
- የታሸገ የታክሲ ሜትር በዓመት አንድ ጊዜ ምርመራ ይደረግበታል። ሜትሩም ሁልጊዜ ሰዎች ሊያዩት በሚችል ቦታ ላይ ሊሆን ይገባል። የተበላሹ ሜትሮች ወዲያውኑ መተካት ወይም መታደስ አለባቸው።
- አንድ የታክሲ ሹፌር ወይም የንግድ አገልግሎት መስጫ መኪና ሹፌር በደንበኞች ጥያቄ መሰረት ብዙ የሚያስከፍሉ መንገዶችን ወይም አቋራጮችን ሊጠቀም ይገባል። በተጨማሪም እያንዳንዱን ጉዞ ሪፓርት ማድረግ፣ ከእያንዳንዱ ጉዞ በኃላ የተረሱ እቃዎች መኪና ውስጥ እንዳሉ ማረጋገጥ፣ ደንበኞቹንና ሞያውን የሚያከብር ጥሩ አለባበስ መልበስ፣ በፍጥነትና በሰዓቱ ደንበኞች ጋር የሚደርስ፣ ለእያንዳንዱ ጉዞ ደረሰኝ የሚሰጥ፣ የመንገደኞችን ዕቃ በመያዝ የሚረዳ፣ በ'ስኬጅዋል ቢ' መሠረት ለደንበኞች የቋሚ ወይም በሜትር የተለካ (fixed or metered rate)፣ መንገደኞች ለተሠጣቸው አገልግሎት በጥሬ ገንዘብ የሚከፍሉ ከሆነ መልሳቸውን በአግባቡ የሚመልስና ከአንድ ዶላር ያልበለጠ የአገልግሎት ክፍያ የሚያስከፍል የዴቢት ወይም ክሬዲት ክፊያ ማሽንን ማቅረብ ይኖርበታል።
- አንድ የታክሲ ወይም የንግድ መኪና አገልግሎት የሚሰጥ ሹፌር የሚከተሉትን ነገሮች በፍፁም ማድረግ የለብትም፤
  - መንገደኞችን ይዞ መብላት ወይም መጠጣት
  - መንገደኞችን ይዞ ሲጋራ ማጨስ
  - ከመንገደኞች ፍላጎት ውጪ ራዲዮ መጠቀም
  - ሌሎች ተሳፋሪዎችን ከየመንገዱ መጫን
  - ከቀበቶ (seatbelts) ቁጥር በላይ ሰዎች መጫን
  - ከ'ስኬጅዋል ቢ' ውጪ ክፍያ መጠየቅ
  - ደረሰኝ መከልከል
  - መኪናው በእንቅስቃሴ ላይ እያለ ክፍያን መውሰድ ወይም መንገደኞችን ማውረድ
  - አጣዳፊ ነገር (emergency) ሳይኖር ስልክና የተለያዩ ኤሌክትሮኒክሶችን መጠቀም
  - የሹፌርን እይታ የሚጋርዱ እቃዎችን መኪና ውስጥ ማስቀመጥ
- አንድ ሹፌር በሚከተሉት ምክኒያቶች ብቻ አገልግሎት መከልከል ይችላል፤
  - ታክሲ የሚለው ምልክት የሚበራ ከሆነ
  - መንገደኛው ለሹፌሩ ያልከፈለው የገንዘብ እዳ ካለበት
  - መንገደኛው አገልግሎት ከሚሰጥ ውሻ ውጪ ከሌላ እንስሳ ጋር የሚጓዝ ከሆነ
  - መኪናውን ሊጎዳ የሚችል ዕቃ እንዲጭን ከተጠየቀ
  - መንገደኛው መኪና ውስጥ ሲጋራ ማጨስ አለብኝ የሚል እቋም ከያዘ
  - የሹፌሩ ደህንነት አደጋ ላይ ከሆነና
  - መንገደኛው ከ100 ዶላር ለሚያስከፍል ጉዞ ቅድመ ክፍያ አልፈፅምም ካለ
- አንድ ሹፌር ለመንገደኛ አገልግሎት ላለመስጠት ከወሰነ ውሳኔውን ለሚሰራበት ድርጅትና ለታክሲ አገልግሎት ተቆጣጣሪ ቢሮ በ24 ሰዓት ውስጥ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።
- የሊሞዚን ሹፌሮች አስቀድመው ለተያዙ ቀጠሮዎች በሰዓቱ በመገኘት መንገደኞችን ማንሳት፣ የቀኑን የጉዞ ዝርዝር መመዝገብ፣ አውሮፕላን ማረፊያው ካልፈቀደ በስተቀር የታክሲ መቆሚያዎች ላይ አለመቆም፣ በቀጠሮ ከሚጠብቋቸው ደንበኞች ውጪ ሌሎችን አለመጫን አለባቸው።
- የታክሲ ወይም የትራንስፖርት አገልግሎት ሠጪ ድርጅቶች የሚያሰሯቸውን ተሽከርካሪዎች የሚከተሉትን ነገሮችን እንዳሟሉ የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው።
  - የታክሲ ወይም የንግድ ፈቃድ
  - ጊዜው ያላለፈ የመኪና ምርመራ ሰርተፊኬት
  - የታሸገ የታክሲ ሜትር

- ከ'ስኬጅዋል ቢ' መሰረት ክፍያ እንደሚፈፅም ማረጋገጥ
- እያንዳንዱ ሹፌር የሹፌር ፈቃድ መያዙን ማረጋገጥ
- በስራ ላይ ያሉ መኪኖችን የሚቆጣጠር የ24 ተቆጣጣሪ መኖሩን ማረጋገጥ

- የታክሲ ድርጅቶች ወይም የግል ድርጅት መኪናቸውን የሚነዱ ሹፌሮች የሚለከቱትን ዝርዝሮች ሊፈፅሙ ይገባል።
  - የንግድ ፈቃዳቸውንና የስራ ማስፈፀሚያ ህጎቻቸው በቢሮአቸው ውስጥ በሚታይ ቦታ ላይ ማኖር
  - ንፁህ የሆነ ስራቸውን የሚያከናውኑበት ቢሮ ወይም ቦታ መያዝ
  - ድርጅቶቻቸው የሚጠቀሙባቸውን የንግድ ስሞች ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ
  - አዲስ የሚገዙ መኪኖችንና ከስራ ውጪ የሚደረጉትን ለሚመለከተው አካል በየጊዜው ማሳወቅ
  - የሁሉንም ሹፌሮች ስም ዝርዝር የያዘ መዝገብ መኖሩን ማረጋገጥ
  - ሁሉም የድርጅቶቻቸው መኪኖች ተመሳሳይ ቀለም እንዳላቸው ማረጋገጥ
  - ከከተማ ውጪ ካሉ ድርጅቶች በስተቀር ሁሉም ከተማ ውሰጥ ያሉ ድርጅቶች 24 ሰዓት የሚሰሩ ሹፌሮች የሚያሰማሩ (dispatching) እንዳላቸው ማረጋገጥ
  - ለሁሉም ሹፌሮቻቸው መኪኖቻቸው ላይ የተገጠሙ መሳሪያዎች እንዴት እንደሚጠቀሙ ሰልጠና እንደተሠጣቸው ማረጋገጥ
  - ጥያቄው ለየት ያለካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም የመንገደኛ ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት
  - ሁሉንም የጉዞ ሰነድ ለ12 ወራት ያህል ማስቀመጥ
  - በውድ ቡፋሎ ግዛት ዲስፓች መቅጠርና
  - ማንኛውንም የገንዘብ ልውውጥ (all financial transactions) በካናዳ ውስጥ መፈፀሙን ማረጋገጥ
- ወደታክሲ ድርጅቶች ወይንም ወደራሳቸው መኪና የሚነዱ ሹፌሮች የሚመጡ ቅሬታዎች የቅሬታ አቅራቢው ስም፤ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥርና የቅሬታዎቹን ዓይነት የያዘ ሊሆን ይኖርባቸዋል። ቅሬታው የቀረበበት ሹፌር የሹፌር ፈቃድ ቁጥርና ቅሬታውን ላቀረበው ሰው የተሰጠው ምላሽ በፅሁፍ ተገልፆ መቀመጥ ይኖርበታል።
- ምንም አይነት የፖሊስ (Peace Officer, Police Officer, Bylaw Officer or Community Peace Officer) ምርመራ ከተደረገ ጉዳዩን ዋናው የታክሲ ተቆጣጣሪ (Chief Taxi Inspector) ሊያውቀው ይጋባል።
- በሹፌሮች ወይንም በመኪኖች ላይ በሚከተሉት ምክኒያቶች የማጣራት ምርመራ ሊደረግ ይችላል፤
  - የአይሮፕላን ማረፊያ እና ሌሎች ፈቃዶች ጊዜያቸው ያላለፈ መሆኑን ለማረጋገጥ
  - የታክሲ ሜትሮች በትክክል መሰራታቸውን ለማረጋገጥ
  - ሹፌሮች ህገ ደንቡን የሚያሟሉ ከሆነ፣ የተሰጣቸው የተሽከረካሪና የሹፌር ፈቃዶች ሊሰርዙ
  - የመኪናው ሜካኒካዊ ሁኔታ በትክክል የሚሰራ መሆኑንና የመኪናውን አጠቃላይ የንፅህና ሁኔታ ለማረጋገጥ
- አንድ ሰው በንግድ ተሽከርካሪ ህገ ደንብ አዋጁ መሰረት በፍርድ ቤት ህግ ወይም በዳኛ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ እስከ 10,000 ዶላር በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ወይም በስድስት ወር እስር ሊቀጣ ይችላል።
- የመቀጫ ቲኬቶች የሚስጡት የንግድ ተሽከርከሪ ህገ ደንቡን በመጣስ ነው። መቀጫዎቹም በ'ስኬጅዋል ቢ' በግልፅ ተቀምጠዋል። ቅጣቱ ፍርድ ቤት መቅረብን የሚጠየቅ ካልሆነ ቅጣቱ የሚጠይቀውን ገንዘብ በፍቃደኝነት መክፈል ይችላል።
- ታክሲው በእንቅስቃሴ ላይ እያለ ለመጀመሪያው 52 ሜትር 3 ዶላር ከ80 ሳንቲምና በሚቀጥሉት እያንዳንዱ 52 ሜትር ጉዞዎች 10 ሳንቲም ሜትሩ ይቆጥራል።
- በመንገደኛው ጥያቄ መሰረት ታክሲው መንገደኛውን ቆሞ የሚጠብቅ ከሆነ በደቂቃ 60 ሳንቲም ወይም በሰዓት 36 ዶላር መንገደኛው እንዲከፍል ይገደዳል።
- ከፎርት ማክመሪ ከተማ ውጪ ለሚደረጉ ጉዞዎች የተተመነ ክፍያ የመንገደኛው ምርጫ ይሆናል።
- ከአንዛክ ወይም ኮንክሊን ለሚጀምሩ ወይም ለሚፈፀሙ ጉዞዎች በ'ስኬጅዋል ቢ' መሠረት የተተመነ ክፍያ ማድረግ ይገባል።